በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ - ሰይጣን እየሠራ ነው!

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሰኔ ፫ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## የመቻቻል ማኅበረሰብ

- መቻቻል የዘመናዊ ማኅበረሰብ ሞራላዊ ደረጃውን የሚጠቁም ብቸኛ ቋንቋ እየሆነ ይገኛል፡፡
- የአሁኑ ማኅበረሰብም የማንኛውንም ሰው አመለካከትና እምነት ከራሳችን ጋር ‹‹እኩል›› አድርገን እንድንቆጥር በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡
- ሁሉም ሃይማኖቶች ወደ አንዱ እግዚአብሔር የሚጠቁሙ የተለያዩ መንገዶች ናቸው ተብሎ እየተነገረን ነው፡፡

## እውነት

- የተረጋገጠ የማያከራክር ጭብጥ ወይም መንገድ ማለት ነው፡፡
- እውነት በአጠቃላይ ነገሮች የሆኑበት ትክክለኛ ገጽታ ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ ሦስት ሰዎችን 2+2 ስንት እንደሆነ ብንጠይቅና ሦስት የተለያየ መልስ ይዘው ቢቀርቡ ቢያንስ ከሦስቱ አንዱ ትክክለኛውን መልስ የማግኘት ዕድል እንዳለው እርግጠኛ ብንሆን ሁለቱ ግን እንደተሳሳቱ እንደርስበታለን፡፡ ምናልባት ሦስቱም ሊሳሳቱ ይችላሉ፡፡ ነገር ከአንድ በላይ ትክክለኛ መልስ አይሰጡም፡፡ ስህተታቸው ግን ብዙ ዓይነት (2+2=5፣ 2+2=6፣ ወዘተ) ቢሆንም መልሱ ግን አንድና ጠባብም ነው፡፡

## እውነት አንጻራዊ ናትን?

- ላንተ የሚሠራ ነገር ነው በሚል አቀራረብ እውነት የሰዎች ግላዊ አመለካከትና ምርጫ እንደሆነ አድርጎ ኅብረተሰቡ ሊያምን ይችላል፡፡ ነገር ግን ብናምንም ባናምንም እውነት በሕይወታችን የምታሳድረው ተጽእኖ አለ፡፡ እውነትም አንጻራዊ(Relative) ሳትሆን ፍጽምት(Absolute) ናት፡፡

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ (The New Age Movement)

- የዚህ እንቅስቃሴ አራማጆች የሰው ዘር እያንዳንዱ አምላክ እንደሆነ መረዳትም ሆነ ማረጋገጥ የሚችልበት ጊዜ ላይ መደረሱን ይጠቅሳሉ።
- ይህም ሙሉ በሙሉ ሲከናወን በአዲሱ ዘመን (New Age) በዓለም ላይ አንድ መንግሥት፣ አንድ ሃይማኖት በአንድ ፍቅር በዓለም ይመሠረታል። በዚህም ጊዜ ጥላቻ፣ አመጽ፣ ጦርነት፣ ወንጀል፣ ዘረኝነት ከዓለማችን ይወገዳል። ሰውም ያለበሽታና ያለሞት በሰላም ይኖራል... ይላሉ።
- በዚህ ወቅት የዚህ እንቅስቃሴ ተጠቂ ከሆኑት Shirley Mclaine ከሴሚናሪዋ መጻሕፍትዋና ቲቪ ዝግጅትዋ ጋር፣ Marilyn Ferguson ታዋቂ ከሆነው የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መጽሐፍ ጋር፣ John Lenon, Oprah Winfrey, Eckart ወዘተ ተጠቃሽ ናቸው።

## የእምነታቸው መሠረት

- በሞኒዝም ያለው ሁሉ ከአንድ መለኮታዊ ኃይል ተገኘ፤ ሁሉም አንድ ነው፡ ሁሉም እግዚአብሔር ነው ይላሉ።
- በፓንቴይዝም ፍጥረት ሁሉ እግዝአብሔር ነው፤ እግዚአብሔርም ፍጥረቱን ሁሉ ነው ይላሉ።
- በፓነንቴይዝም እግዚአብሔር በሁሉ ሁሉም በእግዚአብሔር ውስጥ አለ ይላሉ።
- በሪኢንቻሪኔሽን ደግሞ ከሞትን በኂላ ዳግመኛ ተወልደን ተመልሰን እንደሰው ሌላ ሕይወት እንመራለን፤ ይህም ሂደት ብዙ ጊዜ ይደጋገምና በመጨረሻ ሕያዋን እንሆናለን ብለው ያምናሉ።

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## የእምነታቸው መሠረት

- ሰዋዊ ኅዳሴ በማምጣት የሚያምኑ ደግሞ ራሳቸውንና ሌላውን መፈወስ የሚያስችል ኃይል በራሳቸው ውስጥ እንደሚገነቡና እንደሚያሳድጉ ያምናሉ፡፡ በማስከተልም በርካታ ሰዎች ይህን መሰል ኃይል ሲጎናጸፉ መላውን ፕላኔት ያቀፈ ኅዳሴ ይደረጋል ይላሉ፡፡
- ሞራልም አንጻራዊ እንደሆነ የሚያምኑ ደግሞ፡-
    - በመልካምና በክፉ ወይም በትክክልና በስህተት መካከል ልዩነት የለም፤
    - በምግባር ጉዳይ ፈራጅ የለም፤
    - ድርጊቶች መልካም ወይም ክፉ ከመሆናቸው ውጪ ተጠያቂነትን አያስከትሉም ንስሐም አያስፈልጋቸውም፤
    - ለራሱ መልካም የሆነውን የሚወስነውም ሰው ራሱ ነው ይላሉ፡፡

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## እንዴት እግዚአብሔርን ይሆናሉ?

- **እግዚአብሔርን መሆን ቀላል ነው ምክንያቱም አንተ ራስህ እግዚአብሔርን ነህና፤ የሚቀርህ ቢኖር ይህን ምሉዕ መሆን በሚያስችሉህ ልምምዶች ማዳበር ብቻ ነው ይላሉ፡፡ የዚህም እንቅስቃሴ ዋና ግቡ ራስን እግዚአብሔር ማድረግ ነው፡፡**
- **እነዚህም ከቀደሙት የጥፋት ትምህርቶችና ልምምዶች የተወሰዱ ናቸው፡፡ በነዚህ ዘንድ ከተለመዱት በስፋት አገልግሎት ላይ ከዋሉት መጠቀሚያዎች ለመጥቀስም** Acupuncture, Zen Buddhism, Yoga, clairvoyance, biofeedback, reincarnation therapies, ouija boards, astrology, tea leaves, dream therapy, holistic healing, parasychologic mystic experiences, telepathy, balancing the yin and yan, hypnosis, meditation, mantras, extraterrestrial beings, herbologists, polarity therapy, reflexology, aromatherapy, therapeutic touching, and homeopathy **ማንሳት ይቻላል፡፡**
- **ይህ እንቅስቃሴ በዘፍጥ** 3:4-5 **እንደተጻፈው ሰይጣን አዳምና ሔዋንን ያሳተባቸው አራት ዘዴዎቹ ውጤት ነው፡፡** ‹‹እባብም ለሴቲቱ አላት። ሞትን አትሞቱም ከእርስዋ በበላችሁ ቀን ዓይኖቻችሁ እንዲከፈቱ እንደ እግዚአብሔርም መልካምንና ክፉን የምታውቁ እንድትሆኑ እግዚአብሔር ስለሚያውቅ ነው እንጂ። ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደ ሆነ፥ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፥ ለጥበብም መልካም እንደ ሆነ አየች ከፍሬውም ወሰደችና በላች ለባልዋም ደግሞ ሰጠችው እርሱም ከእርስዋ ጋር በላ።››
- **እነዚህም አራቱ የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮዎች አትሞቱም፣ ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ፣ እንደ እግዚአብሔር መሆንና መልካሙንና ክፉውን ለይቶ ማወቅ የሚሉ ናቸው፡፡**

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## 1. አትሞቱም

- የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን የምናደርግ ከሆን፣ አመጋገባችንን ካስተካከልን፣ በየጊዜው ማሳጅ የሚደረግልን፣ በአኩፓንቸር የምንጠቀም፣ በአስማት በክሪስታል በፒራሚዶች ወዘተ የሚደረጉ ተአምራትን ካመን ፈጽሞ አንታመምም ብለው ያምናሉ።
- ቁስና መንፈስ አንድ ናቸውና በሂደትም ዘላለማዊነትን እንቀዳጃለን ይላሉ።

## 2. ዓይኖቻችሁ ይከፈታሉ

- የአዲሱን ዘመን እንቅስቃሴ ተቀብላችሁ ስትራመዱ ምን ያህል ኃይል እንዳላችሁ፣ ችግሮቻችሁን የመፍታት አቅማችሁንና በወደፊት ዕድላችሁ የመወሰን አቅማችሁን ትረዳላችሁ ይላሉ።

## 3. እንደ እግዚአብሔር መሆን

- እግዚአብሔር ኃይል ነው እግዚአብሔርም ድንጋዩን ከዋክብቱን… ወዘተ ነው ሰውም በሂደት እግዚአብሔርን ይሆናል፤ ይህም ለዓለም ሰላምን ለምድር ችግርም መፍትሔን ያመጣል ይላሉ።

## 4. ክፉውንና በጎውን ማወቅ

- ሁላችንም አንዲት መንደር ከምትሆን ከዓለም የተገኘን ነን፤ ከሙዚቃው ከወንዙ፣ ከተራራው፣ ከማዕበሉ፣ ከውቅያኖሱ፣ ከበረሃው በምናገኘው መረዳት ሁሉን እንለያለን ይላሉ።

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መጻሕፍት

- Seven Spiritual Laws of Success by Deepak Chopra
- The Other Side and Back by Sylvia Browne
- The Art of Happiness by Dalai Lama, et al
- Mind Medicine by Uri Geller
- Talking to Heaven by James Van Praagh

| ክርስትና | የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ |
|---|---|
| በሥላሴ አንድነትና ሦስትነት ማመን | ፓንቴይዝምና ፓነንቴይዝም |
| ፈጣሪ ፍጥረታትን ፈጠረ | ፈጣሪም ፍጡርም ሁሉም አንድ ነው |
| ትንሣኤ | ዳግም መወለድና ደጋግሞ መኖር |
| ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ | ሰው እግዚአብሔር ነው |
| ሰው ፍጡር እግዚአብሔር ፈጣሪ ነው | ሰውና እግዚአብሔር አይለያዩም አንድ ናቸው |
| ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው | ኢየሱስ እግዚአብሔር ለመሆን በቅቷል |
| ክርስቶስ ለፍርድ ይመጣል | አዲሱ ዘመን ይመጣል |
| | |

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## ማጠቃለያ

- ሻርሊ ማክሌይን ግንባር ቀደም የእንቅስቃሴው መሪ ተዋናይ ነው፡፡
- በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ትንቆላና ሳይንስ እኩል የእምነቱ መገልገያ ሆነው የተወሰዱ ሲሆኑ ፓራሳይኮሎጂ፣ አስትሮሎጂና ኳንተም ፊዚክስ የሃይማኖቱ አስተምህሮ ማጠንጠኛዎቹ ናቸው፡፡
- የዘ ኒው ኸርዝ ጸሐፊ ኤካርት ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር ሲሆን ኦፕራ ደጋፊ ሆና ታገለግላለች፡፡
- እነዚህ ሰዎች ስለ ሃይማኖት (እምነት) የተሳሳተ ግንዛቤ ያላቸው ናቸው፡፡ እምነታቸውም መለኮትን እንደ ሥጋዊ ኃይል ከራሳቸው ውስጥ በመፈለግ የታጠረ ነው፡፡
- ኤካርት ክርስቶስ የሚለውን ስም በማንኛውም ነገር መተካት እንችላለን፣ በውስጣችን ያለው ኃይል በክርስቶስ፣ በቡድሃ፣ በመሐመድ ወዘተ ሊገለጥ ይችላል ይላል፡፡
- አስተምህሮአቸው የበርካታ እምነት ተቋማት አስተምህሮ ተውጣጥቶበት ባሕላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አወቃቀር ያለው አቅጣጫ የያዘ ነው፡፡
- ይህን እንቅስቃሴም በርካታ ሴለብሪቲዎች ያራምዱታል፡ ይደግፉታል፡፡
- የመጀመሪያው የአይሁድ፣ ሁለተኛው ጊዜ የክርስትና የነበረ ሲሆን አሁን 21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ ነው ይሉታል፡፡ ዓላማውም ምዕራባዊ ባህልን በሌላው ዓለም ማስፋፋት ነው፣ የቀለለ አቅጣጫ ለሚፈልጉ ሰዎችም መንገዱን መከተል የቀለለ ይሆንላቸዋል፡፡
- አንዳንድ ሰዎች ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ሰማዕትነት፣ ስለ መንፈሳዊ ሕይወት… የምንከተለውን ሃይማኖታችንን አስተምህሮ የማያውቁ ግራ የተጋቡም ስለሆኑ በቀላሉ በዚህ እንቅስቃሴ ይወሰዳሉ፡፡

# የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

## ማጠቃለያ

- ነጻነትን፣ በራስ አስተሳሰብ መደገፍን፣ እርግጠኛነትን... በተመለከተ ያልተቃና አመለካከት ያላቸው... ጥንታውያን አብያተ ክርስቲያናት በወንዶች አመራር ሥር የወደቁ ሴቶችን የረሱ ናቸው... በሚሉ ውዥንብሮቻቸው የተነሳ ብዙዎች ከእውነት ወጥተው በቀላሉ ወደዚህ ጥፋት ይወሰዳሉ።
- በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ አስተምህሮ የፈለጉትን ነገር የማመንና የመከተል መብት ይሰጣል።
- ሰዎችም መለኮት መሆንን እንደ ቻነሊንግ በውስጣቸው ይፈልጋሉ። ... ይህም ፍለጋ ወደ አንድ ኃይል ያደርሳቸዋል... መላእክት ናቸው ለማለት ይሞክራሉ (ግን ሰይጣን - ሉሲፈር) ነው። ክፉ መናፍስትም ይገዙአቸዋል። እግዚአብሔርንም በግልጥ ይቃወሙታል።
- እንቅስቃሴውን መንፈስና መንፈሳዊነትን በአዲስ መልክ መከታተል ነው፣ የሰውን ስሜትና ፍላጎት በዚህ እናረካለን፣ ሴቶች ከወንዶች ተጽእኖ ነጻ ይወጣሉ፣ በወንድና በሴት መካከል ልዩነት የለም፣ ጸሎት የመዝናናት ሰዓት ነው፣ ኃጢአት - ክፋት - መልካም የሚባሉ ነገሮች የሉም፣ ጤንነትን በተለያዩ መንገዶች ማስጠበቅ ይቻላል - መከራ መቀበል - ቅዳሴ - ጾም ... አያስፈልጉም ይላሉ።
- አስቀድሞ በዓለም የሚታየውን በሽታ፣ ረሐብ፣ ሞት፣ ጦርነት ተከትሎ አሁን ፖለቲካዊና ሳይንሳዊ ሚዛኑን የጠበቀ መፍትሔ በአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ መጥቶልናል ይላሉ።
- ይህ እንቅስቃሴ መደብ፣ ቀለም ዘር ያልለየ ታላቅና አዲስ የወንድማማችነት ኃይልን መመስረቻ ሲሆን አንጻራዊ ሃይማኖትንና ፍልስፍናን ማጥናትን የሚያበረታታ ነው ይሉታል።

**ማጠቃለያ**

## የአዲሱ ዘመን እንቅስቃሴ

- **ይህ እንቅስቃሴ በተለያዩ አገሮች በተለያየ መንገድ በመስፋፋት ላይ ይገኛል፡፡**
- **በዚህ እንቅስቃሴ ወደ ታላቁ የመንፈሳዊነት ደረጃ ለመድረስ እንዲያስችል አደንዛዥ እጾችን መጠቀምንም ያበረታታሉ፡፡**
- **እንግዲህ** ‹‹ ይህ ሕዝብ። ዱለት ነው በሚሉት ሁሉ። ዱለት ነው አትበሉ መፈራታቸውንም አትፍሩ፥ አትደንግጡ። ነገር ግን የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርን ቀድሱት የሚያስፈራችሁና የሚያስደነግጣችሁም እርሱ ይሁን። ›› ***ኢሳ 8፡12-13***
- ‹‹ ሥጋንም የሚገድሉትን ነፍስን ግን መግደል የማይቻላቸውን አትፍሩ፤ ይልቅስ ነፍስንም ሥጋንም በገሃነም ሊያጠፋ የሚቻለውን ፍሩ።›› ***ማቴ 10፡28፡፡***
- ‹‹እኔ ግን የምትፈሩትን አሳያችኋለሁ፤ ከገደለ በኋላ ወደ ገሃነም ለመጣል ሥልጣን ያለውን ፍሩ። አዎን እላችኋለሁ፥ እርሱን ፍሩ።›› ***ሉቃ 12፡5፡፡***
- ‹‹እናንተ ግንበኞች የናቃችሁት፥ የማዕዘን ራስ የሆነው ይህ ድንጋይ ነው። መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና። ›› ***የሐዋ 4፡11፡፡***
- ‹‹ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት የማይታገሡበት ዘመን ይመጣልና፤ ነገር ግን ጆሮቻቸውን የሚያሳክክ ስለ ሆነ፥ እንደ ገዛ ምኞታቸው ለራሳቸው አስተማሪዎችን ያከማቻሉ።›› ***ካል ጢሞ 4፡3፡፡*** **እንደተባልን በማስተዋል ከዚህ የጥፋት መንገድ በሃይማኖት ጸንተን ራሳችንን እንጠብቅ፡፡**

ይቆየን፡፡

For your queries or questions E-mail:

kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :

www.zeorthodox.org